# 3ኛ ትምህርት

*መስከረም 28- ጥቅምት 4 2009 ዓ. ም*  *Oct 8-14*

## ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን?

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ኢዮብ 1፣ ኢዮብ 2፣ 1ኛቆሮ. 4፡9፣ ዘፍ. 3፡1-8፣ ፊሊ. 4፡11-13፣ ማቴ. 4፡1-11፣ ፊሊ. 2፡5-8፡፡

> **መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "እርሱ ግን አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ፤ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፣ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን? አላት፡፡ በዚህ ሁሉ ኢዮብ በከንፈሩ አልበደለም፡፡" ኢዮብ 2፡10

የ ኢዮብ መጽሐፍ ሙሉ ለሙሉ አዲስ የሆነን የህይወት ገጽታ ያሳየናል፡፡ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የሚካሄደውን ታላቅ ተጋድሎ በጨረፍታ ያሳየናል፡፡ ያንንም በማድረግ ይህች ዓለም በመንገዳችን ላይ በምትጥላቸው ግራ የሚያጋቡና አንዳንዴም የሚያስፈሩ ነገሮች ዙሪያ የተሻለ መረዳትን በመስጠት የምናይበትን መነጽር ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን የኢዮብ መጽሐፍ ታላቁ ተጋድሎን እኛ የማንሳተፍበት የሌላ ሰው ጦርነት አድርጎ አያስቀምጥልንም፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ እንደዚያ አይደለም "ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና፡፡" ዮሐ. ራዕይ 12፡12 ሰይጣን

ወደ ምድርና ወደ ባህር ወርዷል፡፡ እኛም የእርሱ እርግማን እጅግ ታላቅ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ከኛ መካከል እንደ ስጋ ለባሽነቱ ያ እርግማን ያልተሰማው ማን አለ? በዚህ ሳምንት እየተፋፋመ ባለው ታላቅ ተጋድሎ

ውስጥ የእኛን ሚና የበለጠ ለማስተዋል የኢዮብን የመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች እናጠናለን፡፡ የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለጥቅምት 5 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

*እሁድ መስከረም 29* *Oct 9*

## ኢዮብ የእግዚአብሔር አገልጋይ

ኢዮብ ምዕራፍ 1ን ያንብቡ፡፡ በተለይም ሰይጣን በኢዮብ ላይ ያቀረበው ክስ ላይ ትኩረት ይስጡ፡፡ ሳይጣን እያለ ያለው ምንድነው? በተዘዋዋሪ ሰይጣን ማንን ነው እየወቀሰ ያለው?

---

---

"እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፣ ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል፡፡" (ኢዮብ 1፡10) የኢዮብ መጽሐፍ የሚጀምረው ጻድቅነቱንና መልካም ባህሪውን ብቻ ሳይሆን ብልጽግናውንና ፍሬያማነቱን በመናገር ነው፡፡ ኢዮብ "በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ

ታላቅ" (ኢዮብ 1፡3) እንዲባል ያስቻሉት እነዚህ መገለጫዎች ነበሩ፡፡ ሰይጣንም በእግዚአብሔር ፊት ይህንን ስለምታደርግለት ነው የሚገለግልህ ያለው እነዚህን ነገሮች ገልጾ ነው፡፡

በሰይጣን ክስ ውስጥ ያለው ዋና ኃሳብ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ከኢዮብ ቢወስድ "በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል፡፡" (ኢዮብ 1፡11) የሚል ነበር፡፡ ጥቃቱ በእግዚአብሔር በራሱ ላይ ነበር፡፡ (የታላቁ ተጋድሎ ዋናው ጉዳይም ይኸው ነው፡፡) እግዚአብሔር እጅግ ድንቅና ቸር ከሆነ ኢዮብ ከፍቅርና ከአድናቆት ብቻ ይታዘዘዋል፣ ያመልከዋል፡፡ ደግሞስ ብዙ ውለታ የዋለለትን አምላክ የማይወድ ማን አለ? ስለዚህ ሰይጣን

እያለ ያለው ኢዮብ ታማኝ እንዲሆን እግዚአብሔር በጥቅም አባብሎታል ነው። ስለዚህ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ከፍቅር የተነሳ ሳይሆን ለራሱ ጥቅም ሲል ነው ብሎ ተሟገተ። እጅግ አምባገነንና ጨካኝ የፖለቲካ መሪዎች አገልጋዮች መሪያቸው ለነርሱ መልካም ስለሆነ እስከሞት ድረስ ለመሪዎቻቸው ታማኝ የመሆናቸውን እውነታ ያሰላስሉ። እግዚአብሔር በእውነትም እንደሚነገረው ቸር፣ አፍቃሪና ግድ የሚለው አምላክ ከሆነ ኢዮብ ያለውን ሁሉ ቢያጣ እንኳን እግዚአብሔርን ያገለግላል።

ሰይጣን ኢዮብ ታማኝ ሆኖ አይቀጥልም ብሎ ሲናገር ኢዮብ እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ እንደማይተማመነውና እስካሁንም ታማኝ የሆነው እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ብቻ ነው ማለቱ ነው። ሰይጣን እንደሚለው ከሆነ በመጨረሻ የኢዮብ ታማኝነት የሚወሰነው እርሱ ከተጠቀመ ብቻ ነው።

**እርስዎ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት ለምንድ ነው? ምናልባት ምክንያትዎ ትክክለኛ ላይሆን ይችላል። (ምክንያትዎ ትክክል ካልሆነ) ትክክለኛ ምክንያት እስኪያገኙ ድረስ መጠበቅ ቢኖርብዎ በእርስዎና በእምነትዎ ላይ ምን ሊፈጠር ይችላል?**

## ቁርበት ስለ ቁርበት፡ ጦርነቱ ቀጥሏል

ኢዮብ 2፡1-3 የሚጀምረው ኢዮብ 1፡6-8ን በመድገም ነው፡፡ ትልቁ ልዩነት የኢዮብ 2፡3 የመጨረሻው ክፍል እግዚአብሔር ራሱ ኢዮብ ያን ያህል መከራ ቢደርስበትም ታማኝ ሆኖ እንደቀጠለ መናገሩ ነው፡፡ ስለዚህ ኢዮብ 2፡3 ጋ ስንደርስ የሰይጣን ክሶች ውሸት መሆናቸው እየተረጋገጠ እነደሆነ እናያለን፡፡ ኢዮብ ሰይጣን ያደርጋል ካለው በተቃራኒ ከመርገም ይልቅ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ቀጠለ፡፡

**ኢዮብ 2ን ያንብቡ፡፡ በነዚህ ጥቅሶች ምንተፈጠረ? በኢዮብ 1 እና 2 ላይ "የእግዚአብሔር ልጆች" የተባሉት በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የተደረገውን ውይይት በምስክርነት መስማታቸው ምን ፋይዳ አለው?**

---

"ቁርበት ስለ ቁርበት ነው" የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ብዙ ተንተኞችን ያነጋገረ ነው፡፡ ሆኖም በኢዮብ በራሱ ላይ አንድ ነገር ይከሰትና ያኔ ታማኝነቱ ይታያል ማለት ነው፡፡ አካሉ ጤናው ይጓደልና የሚሆነውን እናያለን፡፡

አስገራሚው ነገር የተከሰተው ነገር ማንም ሳያይ የሆነ አልነበረም፡፡ በኢዮብ መጽሐፍ እንደተገለፁት ሁለቱም ተጋድሎዎች በእግዚአብሔርና በሰማያዊ ዜጎች መሰባሰብ መካከል የተፈጠረ ነው፡፡ ሰይጣን ክሱን በገሃድ በእግዚአብሔርናባልወደቁ ፍጥረታት መካከል አወጀው፡፡ ይህ ኃሳብ ስለ ታላቁ ተጋድሎ ከምናውቀው ኃሳብ ጋር ይገጥማል፡፡ በዓለማት ሁሉፊት እየተከናወነ ያለ ነገር ነበር (1ኛቆሮ. 4፡9፣ ዳን. 7፡10፣ ራዕይ 12፡7-9ን ያንብቡ)

"ነገር ግን የደህንነት ዕቅድ ከሰው ልጅ ደህንነት የሰፋና የጠለቀ ዓላማ ነበረው፡፡ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለዚህ ብቻ አልነበረም፡፡ የዚህች አነስተኛ ምድር ነዋሪዎች የእግዚአብሔር ሕግ መታየት እንዳለበት ያመለከቱት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለመላው ዩኒቨርስ የእግዚአብሔርን ባህሪ እንከን በሌለው መልኩ ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ነበር፡፡ . . . ክርስቶስ ለሰው ልጅ ደህንነት ሲል የፈፀመው ድርጊት ሰማይን ለሰዎች ማስገኘት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አብ እና ወልድ ከሰይጣን አመጻ ጋር በተጎዳኘ ሳደረጉት ሁሉ በዩኒቨርስ ፊት ጻድቅነታቸውን ይመሰክራል፡፡

በመሆኑም የእግዚአብሔርን ሕግ ዘላለማዊነት በማጽናት የኃጢአትን ተፈጥሮና ውጤት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡" የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገፅ 66፣67/በአማርኛው/

*ማክሰኞ ጥቅምት 1* Oct 11

## የእግዚአብሔር ስም ይባረክ

**ሰይጣን በኢዮብ ላይ የመጀመሪያውን ጥቃት ከፈፀመናየመጣበትን ችግር ዜና ከሰማ በኋላ ኢዮብ በምን መልኩ መልስ ሰጠ? (ኢዮብ1፡20-22) በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ሆኖም ኢዮብ "ኃጢአት አለመስራቱ እግዚአብሔርንም አለመክሰሱ" ምን ያስተምረናል?**

---

በፍቅር ላይ የተመሠረተው የእግዚአብሔር መንግስት ማዕከልየምርጫ ነፃነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ተገደን

ሳይሆን ስለምንወደው እንድናገለግለው ይፈልጋል። "ሰይጣን ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ለራሱ ጥቅም ሲል እንደሆነ ተከራከረ። . . . እውነተኛ ሃይማኖት ከፍቅርና የእግዚአብሔርን ባህሪ ከማድነቅ መሆኑን፣ ለሽልማት ሳይሆን እምነቱን ከመውደድ የተነሳ እንደሆነ ለመካድ ሞከረ። እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት በሰማይ የሚያገኙትን ብዙ ክብር አስበው ሳይሆን መገልገል የሚገባው በመሆኑ ብቻ እንደሆነና የሚወዱትም ስለሚባርካቸው ሳይሆን ሊወዱትና ሊታመኑት የሚገባው በመሆኑ እንደሆነ ለመካድ ሞከረ።" *The SDA Bible Commentary, Vol.3P.500*

በኢዮብ መጽሐፍ ኢዮብ የሰይጣን ክስ ስህተት መሆኑን አረጋግጧል። እግዚአብሔር ምን እንደሚፈጠር አስቀድሞ ቢያውቅም ኢዮብ የመጣበትን ነገር በሌላ መልኩ ሊያስተናግደው ይችል ነበር። ኃጢአት ሊሰራ በእግዚአብሔርም ላይ ሊያጉረመርም ይችል ነበር። ኢዮብ እንደዚያ እንዲሆን እግዚአብሔር አላስገደደውም። ከነበረበት ሁኔታ አንፃር የፀና ታማኝነቱ በሰዎችና በመላዕክት ፊት አስገራሚ ምስክርነት ነበር።

**በኢዮብ ምዕራፍ 1 የተፈጠረውንና በዘፍጥረት 3፡1-8 በአዳምና ሔዋን የተከሰተውን ያነፃፅሩ። ይህ ንፅፅር ኃጢያታቸውን የከፋ የሚያደርገው እንዴት ነው?**

---

---

አዳምና ሔዋን በኃጢአት አልባዋ እውነተኛ ገነት ውስጥ በሰይጣን ጥቃት ምክንያት በኃጢአት ወደቁ፤ ኢዮብ ግን በብዙ ህመምና ስቃይ ውስጥ የሰይጣንን ውጊያ ተቋቁሞ ለጌታ ታማኝ ሆነ።ሁለቱም ክስተቶች የምርጫ ነፃነት ምን ያክል ታላላቅ ጉዳዮች ላይ መወሰን የሚያስችል መሆኑን የሚያሳዩ ግሩም ምሳሌዎች ናቸው።

**የኢዮብ ምላሽ እኛለኃጢአታችን በአብዛኛው የምንሰጣቸው ሰበቦች ርካሽ፣ ቀላልና ውሸት መሆናቸውን የሚያሳየው እንዴት ነው?**

# የኢዮብ ሚስት

በኢዮብ ታሪክ ስለሌላዋ ገፈት ቀማሽ ስለሚስቱ ለማውራት አሁን የተሻለ ጊዜ ነው። የምናገኛት በኢዮብ 2፡9-10 ላይ ነው። ከዚያ በኋላ በታሪኩ ውስጥ አናገኛትም። ስለሷ ሌላ ተጨማሪ ነገር አልተነገረንም። ሆኖም ከተፈጠሩት ነገሮች አንፃር ይህችምስኪንሴት ያለፈችበትን መከራ ማን ሊያስተውል ይችላል? የልጆቿና በምዕራፍ 1 ላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ መጥፋት የስቃይዋን ብዛት ይናገራሉ። ሁላችንም በታላቁ ተጋድሎ ውስጥ ተሳታፊዎች ነን ከዚህ ማንም አያመልጥም።

ኢዮብ 2፡3ንና 2፡9ን ያነፃፅሩ። ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ ኢዮብ ሚስት የተጠቀሰ ምን የጋራ ሃረግ አለ? የሁለቱ አጠቃቀም ምን ጠቀሜታ አለው?

---

በሁለቱም ጥቅሶች ኢዮብ ሃቀኛ ሆኖ ስለመፅናቱ መጠቀሱ በድንገት አይደለም። "ሃቀኛ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በኢዮብ 1፡1ና 1፡8 ላይ ከተጠቀሰው በአብዛኛው "ነቀፋ የሌለበት" ተብሎ ከተተረጉመው ተመሳሳይ ቃል የመጣ ነው። ስርወ ቃሉ "ሙሉ የሆነ" የሚል አንድምታ ያለው ነው።

የኢዮብ ሚስት እግዚአብሔር ኢዮብን ባወደሰበት በዚያው መልካም ባህሪ ላይ ኢዮብን መገዳደሯ የሚያሳዝን ነው። በሃዘኗና በለቅሶዋ እግዚአብሔር ኢዮብ አያደርግም ብሎ የተከራከረለትን ነገር እንዲያደርግ ገፋፋችው። ምንም እንኳን እሷ ላይ ባንፈርድም በሌሎች ላይ የማሰናከያ ድንጋይ እንዳንሆን የሚያስጠነቅቀን መልካም ትምህርት ሰጥቶናል (ሉቃስ17፡2) ።

**ኢዮብ 2፡10ን ያንብቡ። ኢዮብ በዚህ ቦታ ምን አይነት ምስክርነት እየሰጠ ነው? /በተጨማሪም ፊል. 4፡ 11-13ን ያንብቡ/**

ኢዮብ የእምነቱን እውነተኛነት አረጋገጠ፡፡ በመልካምም በመጥፎም ጊዜ እግዚአብሔርን እንደሚያመልክ አረጋገጠ፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ሰይጣን አሁን ከታሪኩ ጠፋ፤ ዳግም አልተጠቀሰም፡፡ ምንም እንኳን ባይፃፍልንም በኢዮብ ምላሽ ሰይጣን ምን ያክል ሊናደድና ተስፋ ሊቆርጥ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ደግሞም አዳምና ሔዋንን እንዲሁም ሌሎች ብዙዎችን እንዴት በቀላሉ እንደጣለ ያስታውሱ፡፡ "የወንድሞች ከሳሽ"(ራዕይ 12፡10)ከኢዮብ ሌላ የሚከሰው ሰው መፈለግ ይኖርበታል፡፡

**በመልካምም ሆነ በክፉ ጊዜ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?**

*ሐሙስ ጥቅምት 3* *Oct 13*

## እስከሞት መታዘዝ

"በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፤ በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ አልተናገረም፡፡" ይላል ኢዮብ 1፡22፡፡ ኢዮብ 2፡ 10 ደግሞ "በዚህ ሁሉ ኢዮብ በንግግሩ አልበደለም" ይላል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ብዙ ጥቃት ቢደርስበትም ኢዮብ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ቀጠለ፡፡ ሁለቱም ጥቅሶች ኢዮብ በተግባርም ሆነ በቃላት አለመበደሉ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡

በእርግጥም ጥቅሶቹ ኢዮብ ኃጢአተኛ አልነበረም አላሉም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆንን ይናገራል፤ ኃጢአት አልሰራንም ብንል እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም /1ኛዮሐ. 1፡10/ ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን እግዚአብሐርን የሚፈራ ከክፋት የራቀ /ኢዮብ 1፡1/ የሚለው መግለጫ ኃጢያት አልባ ነው ማለት አይደለም። ልክ እንደማንኛውም ሰው ኢዮብ በኃጢያት የተወለደና አዳኝ የሚያስፈልገው ነበር።

ያሁሉ ችግር መጥቶበትም ለአምላኩ ታማኝ ሆኖ ቀጠለ። ከዚህ አንፃር ኢዮብ ምንም አይነት መከራ ቢመጣበትም በኃጢያት ያልወደቀውን ኢየሱስን የሚያመላክት ምሳሌ ሆኖ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ የሰነዘረውን ክስ ውድቅ አደረገ። በእርግጥ ኢየሱስ ያደረገው ኢዮብ ካደረገው ይልቅ ታላቅና ሰፊ ውጤት የነበረው ነው። ሆኖም መመሳሰላቸው እንዳለ ነው።

**ማቴዎስ 4፡1-11ን ያንብቡ። የኢዮብ ልምምድ በዚህ ቦታ ከተፈጠረው ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?**

___

___

በከባድ ሁኔታ፣ በምግብ እጦት ሰውነቱ ደክሞ ኢየሱስ "በኃጢአተኛ ሰው አምሳል" /ሮሜ.8፡3/ ሆኖ ልክ እንደ ኢዮብ ሰይጣን እንዲያደርግ የፈለገውን ነገር አላደረገም። ኢዮብ ታማኝነቱን ሲያፀና የሰይጣን ጉዳይ ከምስሉ እንደጠፋ ሁሉ ኢየሱስ የሰይጣንን ፈተና እንዳሸነፈም በማቴ. 4፡11 "ዲያቢሎስ ትቶት ሄደ" ተብሎ ተፅፏል። /ያዕቆብ 4፡7ንም ጨምረው ያንብቡ።/

ሆኖም የሱስ በምድረበዳ የተጋፈጠው ነገር ገና የታሪኩ ጅምር ነበር። የርሱ ከባዱ ፈተናበመስቀል ከሞት ጋር ተፋጦ ሁሉም ነገር በርሱ ላይ ቢወረወርም (ከኢዮብም በባሰ መልኩ) እስከመጨረሻው ታማኝ ሆኖ የቆመበት ታሪክ ነው።

**ፊሊጲስዮስ 2፡5-8ን ያንብቡ። የክርስቶስ "እስከ ሞት ታዛዥ መሆን" ምን ተስፋ ይሰጠናል? ከርሱ ተምረን እንዴት መኖር እንዳለብን ይህ ምን ይነግረናል?**

## ተጨማሪ ሀሳብ

የዕብራይስጡን ትርጉም የሚመረምሩ የኢዮብ መፅሐፍ ተማሪዎች አንድ አስገራሚ ነገር ያያሉ። የኢዮብ ሚስት ለኢዮብ የተናገረችው "እግዚአብሔርን እርገምና ሙት" /ኢዮብ 2:9/ ተብሎ ተተርጉሟል።

ኢዮብ 1:5 ደግሞ "ምናልባት ልጆቼ ኃጢአት ሰርተው እግዚአብሔርን በልባቸው ረግመው ይሆናል።" ተብሎ ተተርጉሟል። እንዲሁም ኢዮብ 1:11 እስቲ እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ንካበት፤ በርግጥ በፊት ለፊት ይረግምሃል።" ተብሎ ተተርጉሟል። ሆኖም በሁሉም ሁኔታዎች መርገም ተብሎ የተተረጎመው ቃል መባረክ የሚል ትርጉም ካለው ቃል የተወሰደ ነው። ባራክ (brk) የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የተተረጎመው መባረክ ተብሎ ነው። በዘፍጥረት 1:22 ላይ እግዚአብሔር የሰራቸውን ፍጥረታት ሁሉ "ሲባርክ" በጥቅም ላይ የዋለው ይህ ቃል ነው። በመዝሙር 66:8 "ሕዝቦች ሆይ፤አምላካችንን ባርኩ።" በሚለው ጥቅስ ውስጥ "ባርኩ" የሚለው ቃል የተተረጎመው ከተመሳሳይ ስርወ ቃል ነው።

ታዲያ "መባረክ" የሚል ትርጓሜ ያለው ቃል በነዚህ ጥቂት ጥቅሶች ውስጥ እንዴት "መርገም" ተብሎ ተተረጎመ? በመጀመሪያ ደረጃ በነዚያ በኢዮብ ውስጥ በሚገኙ ጥቅሶች ውስጥ "መባረክ" የሚባለው ቃል ጥቅም ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ ትርጉም አይሰጥም ነበር። በኢዮብ 1:5 ላይ ልጆቹ ምናልባት በልባቸው እግዚአብሔርን "ባርከው" ቢሆን ኖሮ መስዋዕት ማቅረብ ለምን ያስፈልገዋል? አውዱ የተለየ

ትርጓሜ ለመጠቀም ያስገድዳል። በኢዮብ 1:11ና 2:5 ላይም ተመሳሳይ ነው። አውዱ የቃሉ ትርጉም "መርገም" እንዲሆን ያስገድዳል። ደግሞስ ኢዮብ ሚስቱ እግዚአብሔርን ባርክ ብትለው ለምን ይገስፃታል? ታሪኩ ትርጉም የሚሰጠን ቃሉ "መርገም" ተብሎ ከተተረጎመ ነው።

ታድያ ፀሐፊው "መርገም" በሚለው ቃል ፈንታ የተሻሉና የተለመዱ ቃላትን ለምን አልተጠቀመም? እግዚአብሔርን የመርገም ፅንሰ ሐሳብ ለፀሐፊው መንፈሳዊ ማህበረሰብ የሚያስከፋ ነገር ስለነበር የመፅሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎች ቃሉ ዘወር ያለ እንደሆነ ያምናሉ (ተመሳሳዩ ባራክ የሚለው ቃል በ1 ነገስት 21፡10፣13 ላይ መስደብ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡) ስለዚህ ሙሴ "መርገም" የሚል አንድምታ ያለውንሳይሆን "መባረክ" የሚል አንድምታ ያለውን ቃል ከአውዱ ተነስቶ "መርገም" ብሎ ተረጉመው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. በችግር ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖርና ማንነቱን በጥያቄ ውስጥ ማስገባት የሚቀናቸው ለምን ይሆን? በወደቀችና ታላቁ ተጋድሎ በግልፅ በሚታይባት አለም የመስቀሉን እውነታ ሁልጊዜ ከፊታችን ማድረግ የሚኖርብን ለምንድን ነው?
2. እስከምናውቀው ድረስ በኢዮብ ላይ እየተካሄደ የነበረውንነገር እኛ ብናውቅም ኢዮብ ግን አያውቅም ነበር፡፡ እሱ የሚያውቀው ያጋጠሙትን ችግሮች ነበር፡፡ ትልቁን ምስል አላየም፡፡ ታድያ ከዚህ እኛም በችግር ውስጥ ብንሆን የማናየው ወይም የማናስተውለው ትልቅ ምስል እንዳለ ማስታወስ ያለብን ለምንድን ነው? ይህንን ማስታወሳችን መፅናናት የሚሰጠን እንዴት ነው?